ማለዳ ላይ ወይም ከቀትር በኋላ ወደ መስጂድ የሄደ ሰው ማልዶ በሄደና ከቀትር በኋላ በሄደ ቁጥር አላህ ለርሱ ጀነት ውስጥ መስተንግዶ ያዘጋጅለታል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል: "ማለዳ ላይ ወይም ከቀትር በኋላ ወደ መስጂድ የሄደ ሰው ማልዶ በሄደና
ከቀትር በኋላ በሄደ ቁጥር አላህ ለርሱ ጀነት ውስጥ መስተንግዶ ያዘጋጅለታል።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ለአምልኮም ይሁን ለእውቀት ወይም ከዚህ ውጪ ላሉ መልካም አላማዎች በመጀመሪያው የቀን ክፍልም ሆነ በመጨረሻው የቀን ክፍል በማንኛውም ወቅት መስጂድ የመጣ ሰው በቀኑ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ወይም በሌሊቱ ክፍለ ጊዜ ውስጥ መስጂድ በመጣ ቁጥር አላህ ለርሱ ጀነት ውስጥ ስፍራና መስተንግዶ እንዳዘጋጀለት አበሰሩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5436